አፍሪካ ቲቪ

14

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

በቴሌግራም

4

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# سُورَةُ العَلَقِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

ٱقۡرَأۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلَّذِي خَلَقَ ١ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِنۡ عَلَقٍ ٢ ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ٤
عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ٥ كَلَّآ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَيَطۡغَىٰٓ ٦ أَن رَّءَاهُ ٱسۡتَغۡنَىٰٓ ٧ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجۡعَىٰٓ ٨
أَرَءَيۡتَ ٱلَّذِي يَنۡهَىٰ ٩ عَبۡدًا إِذَا صَلَّىٰٓ ١٠ أَرَءَيۡتَ إِن كَانَ عَلَى ٱلۡهُدَىٰٓ ١١ أَوۡ أَمَرَ بِٱلتَّقۡوَىٰٓ ١٢ أَرَءَيۡتَ
إِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰٓ ١٣ أَلَمۡ يَعۡلَم بِأَنَّ ٱللَّهَ يَرَىٰ ١٤ كَلَّا لَئِن لَّمۡ يَنتَهِ لَنَسۡفَعَۢا بِٱلنَّاصِيَةِ ١٥ نَاصِيَةٖ كَٰذِبَةٍ
خَاطِئَةٖ ١٦ فَلۡيَدۡعُ نَادِيَهُۥ ١٧ سَنَدۡعُ ٱلزَّبَانِيَةَ ١٨ كَلَّا لَا تُطِعۡهُ وَٱسۡجُدۡ وَٱقۡتَرِب ۩ ١٩



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ከሱረቱል ዐለቅ ከ(4)ኛው አንቀፅ ጀምሮ የወረደበት ምክንያት፡-በአንድ ወቅት ያ! የዚህ ኡመህ ፈርዖን በመባል የሚታወቀው አቡ ጀህል ለህዝቦች በእውነት እያያችሁት ሙሐመድ ፊቱን በመሬት ላይ ይደፋልን ብሎ ሲጠይቅ አዎ ሁል ጊዜ አይደል የሚሰግደው አሉት፡፡ እሱም እኔ እያ የሁት ካደረገ ግን አንገቱ ላይ እቆማለሁ፡፡ ወይም ፊቱን በአፈር ላይ አልሞሰምሰዋለሁ፡፡ አለና አንድ ቀን ነብዩ صلى اللّٰه عليه وسلم እየሰገዱ ባሉበት ወቅት ያለዉን ሊተገብር ወደ እሳቸው መጥቶ ይህን ነገር ተው አላልኩህም? ሲላቸው ነብዩ ﷺ, ስለ ተቆጡት በዚህ አገር አንድም ከእኔ የተሻለ ቡድን ያለው እንደሌለ ታውቃለህ፡፡ እንዴት ደፍረህ ትናገራለህ? አላቸው በዚህ ላይ እያለ ራሱን መቆጣጠር በማይችልበት መልአክ ፊት ለፊቱ ቆሞ ሲያስፈራራው ወደ ኋላ ሲሸሽ ና በእጁ ሲከላከል ያዩት ሰዎች ምነው ብለው ሲጠይቁት በኔና በሱ መካከል የእሳት ጉድጓድ ነበረ የሚያስፈራራ ነገርም ነበረ በማለት ተናገረ፡፡ ነብዩም ስለዚህ ነገር ሲናገሩ ወደኔ ቀርቦ በነበረ መላይኮች አካሎቹን በተከፋፈሏቸው ነበር ብለዋል፡፡ ይህን ታሪክ አስመልክቶ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት፡፡

(አህመድ፤ ሙስሊምና ሱዩጢ)

- በተጨማሪም ያ! ሰውን ከዚያ ደካማ ከሆነ ፈሳሽ የፈጠረው ጌታ አላህ መግሪያና መግባቢያ የሆነውን መጻፍና እንዲሁም ያለወቃቸውን ነገሮች እንዲያስተምረው ያስገነዝባል፡፡
- ሀብትና ጉልበት የአላህን ህግ እንዲጣስ ከሚገፋፉ ነገሮች መካከል መሆናቸውንና ሁሉም ወደ አላህ እንደሚለስ ያስታውስና ከአላህ መንገድ እንቅፋት የሆኑትን ሁሉ በማስፈራራት ቅንጥ ቅንጣቸውን በማስያዝ ወደ ገሀነም ሊያወርዳቸው እንደሚችል አስፍራርቶ በዚያ ዕለት ምንም ረዳት እንደማይኖር መክሮ የአላህን ህግ ለሚያስከብሩ ሁሉ አመፀኞችን እንደመስሉ ጥሪ በማስተላለፍ
 መልዕክቱን ያጠቃልላል፡፡

- (6) በእውነቱ እንደ አቡጀህል ያለው ጠማማ ሰው የአላህን ወሰን በማለፍ ወሰን አላፊ ይሆናል፡፡
- (7) ይህም የሆነው ባለው ገንዘብና ስልጣን የተብቃቃ መስሎ ስለታየው ነው፡፡
- (8) አንተ የሰው ልጅ ሆይ! በትንሳኤው ቀን ወደ ጌታህ ተመላሽ ነህ፡፡ እያንዳንዱንም እንደየሥራው ይመነዳዋል፡፡
- (መመለሻው ወደ ጌታህ ብቻ ነው፡፡)

- (9) በመከልከል ደረጃ (ከአቡጀህል) የበለጠ የሚገርም ሰው አይተሀልን?!
- (10) ባሪያችንን ሙሐመድን (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ካዕባ ዘንድ ሲሰግድ ከሚከለክለው የበለጠ።
- (11) እስቲ ንገረኝ ለመሆኑ ያ የሚከለከለው ሰው ስለ ጌታው በእውነተኛና ትክክለኛ ጎዳና ላይ ቢሆንስ?!
- (12) ሰዎችን አላህን ትእዛዙን በመፈጸምና የከለከለውን በመከልከል እንዲፈሩ የሚያዝ ቢሆንስ? እንዲህ ዓይነት ሰው ሊከለከል ይገባዋልን?!

- (13) ያ ከልካይ የሆነው ሰው መልዕክተኛው ይዞት የመጣውን ነገር ያስተባበለና ያመፀ መሆኑ አይገርምህምን?! ለመሆኑስ አላህን አይፈራምን?!
- (14) ይህንን የሚሰግደውን ባሪያ የሚከለክለው ሰው አላህ ይህንን ተግባሩን የሚያይ መሆኑን አያውቅምን?! እሱ ምንም ነገር አይሰወርበትም።

አፍሪካ አካዳሚ

- (15) ይህ ማንም እንደሚገምተው አይደለም! ባሪያችንን ከማወክና እሱን ከማስተባበል የማይታቀብ ከሆነ አናቱን ብርቱ የሆነ አያያዝን ይዘን እየጎተትን ወደ እሳት እንወረውረዋለን።
- (16) የዚህ አናት ባለቤት በንግግሩ ሀሰተኛ በተግባሩ ስህተተኛ ነው።
- (17) መሃል አናቱን ይዘን እሳት ውስጥ ስንወረውረው ከቅጣት ለማዳን ይረዱት ዘንድ ጓደኞቹንና ግብረ አበሮቹን ይጥራ።

አፍሪካ አካዳሚ

- (18) እኛ የጀሀነም ጠባቂ የሆኑትን የአላህን ትእዛዝ ከመፈፀም የማያምፁና ያዘዛቸውን የሚፈፅሙ የሆኑ ጨካኝ መላእክቶችን እንጠራለን። የትኛው ጠንካራና አሸናፊ እንደሚሆን ይታያል።
- (19) ይህ በዳይ የሆነ ሰው አንተን ለመጉዳት እንዳሰበው አይሳካለትም። እሱን አትታዘዘው፤ ለአላህም ስገድ፤ ትእዛዙንም በማክበር ወደ እርሱ ተቃረብ፤ በእርግጥም ወደ አላህ ያቀርብሀል።

- ከሱረቱል ዐለቅ (ከረጋ ደም ምዕራፉ) ከ (1-19) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-
- 1. ስለ ወህይ አጀማመርና የነብዩ صلى الله عليه وسلم ነብይነት እንዴት እንደተከሰተና እንዴት እንደተጀመረ፤
- 2. የአላህን ውዴታ ማግኘት የላቀ ግብ መሆኑን።
- 3. ማንበብና መፃፍ እስልምና ውስጥ ወሳኝ መሆኑን።
- 4. ሀብት ወደ ኩራት እና ከእውነት ወደ መራቅ የሚያመራ ከሆነ አደጋ መሆኑን።
- 5. መልካም የተባለን ሁሉ በአላህ ስም የመጀመር ምንዳ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን፤
- 6. በመህፀን ውስጥ የሰው ልጅ ሼል እድገትን በተመለከተ ሰፊ መግለጫ፤......

- 7. የአላህ ቸርነት ከሁሉ የበለጠ መሆኑ፤
- 8. ስለ መፃፍና ስለ መፃፊያ በዚህ በጨለመ ዘመን ማስታወሱና ክብር የሚገባው መሆኑን መጠቆም፤
- 9. አላህ የሰውን ልጅ የማያውቀውን በማሳወቁ የዋለለትን ከፍተኛ ውለታ ማስታወስና ማመስገን እንደሚገባ፤
- 10. የሰው ልጅ ባህሪ እምነት ከሌለው ምን እንደሚመስል፤
- 11. ሰውን ከመልካም ነገር መከልከል የከሀዲ መገለጫ ባህሪ መሆኑን።
- 12. አላህ መልዕክተኛውን ሙሐመድ صلى الله عليه وسلم በገሀድ እንደሚረዳ ቃል መግባቱን፤
- 13. ነብዩን صلى الله عليه وسلم ከሁሉም በበለጠ ያሰያቃቸው የነበረውንና የዚህ ኡመት ፈርዑን ያሉትን አቡጀህልን አላህ እርግማን ያውርደበት መሆኑን በግልፅ እንማራለን፡፡